## የይግባኝ መብቶች (APPEAL RIGHTS)

**በድጋሚ ማየት(Reconsideration)፡-** የአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ (Administrative Law Judge, ALJ) ይህን የመጨረሻ ትእዛዝ በድጋሚ እንዲያዩት የመጠየቅ መብት አለዎት። የWashington የተሻሻለው ኮድ (Revised Code of Washington, RCW) 34.05.470 እና የWashington አስተዳደራዊ ኮድ(Washington Administrative Code, WAC) 388-02-0605። ጥያቄዎ በጽሑፍ መሆን እና የመጨረሻ ትዕዛዙ በደብዳቤ ከተላከ በአስር (10) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ለALJ መድረስ አለበት። ለዳግም እንዲታይ ቅጽ የተካተተውን ጥየቄ ሊጠቀሙ ይችላሉ። በድጋሚ እንዲታይ የቀረበው ጥያቄ በዚህ አስር ቀናት ውስጥ ካልደረሰ፣ በድጋሚ አይታይም እና የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምገማ ለመጠየቅ የተቀመጠው ቀነ ገደብ መሄዱን ይቀጥላል። ጥያቄዎን ለመኪተለው አድራሻ ይላኩ፡-

የአስተዳደራዊ ችሎቶች ቢሮ
PO Box 42489 Olympia, WA 98504
ስልክ:- (800) 845-8830
ፋክስ፡-

በድጋሚ እንዲታይ የቀረበው ጥያቄ ወቅታዊ ከሆነ፣ ALJ ጥያቄውን ለመወሰን ወይም ለእርስዎ እና ለሌሎች ወገኖች ALJ ጥያቄውን የሚወስንበትን ቀን የሚገልጽ የጽሑፍ ማስታወቂያ በደብዳቤ ለመላክ ሃያ (20) ቀናት አላቸው። በሃያ ቀናት ጊዜ ውስጥ በALJ ምንም ዓይነት እርምጃ ካልተወሰደ በድጋሚ እንዲታይ የቀረበው ጥያቄው ውድቅ ይሆናል። ጥያቄው ወቅታዊ ከሆነ፣ የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምገማ ለመጠየቅ የተቀመጠው የጊዜ ሰሌዳ የሚጀምረው በድጋሚ የመታየት ትዕዛዙ በደብዳቤ በተላከበት ቀን ነው።

**የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምገማ(Superior Court Review)፡-** እንዲሁም የመጨረሻ ትዕዛዙ በደብዳቤ በተላከበት ሰላሳ (30) የቀን መቁጠሪያ ቀናት ውስጥ ይህን የመጨረሻ ትዕዛዝ ለበላይ ፍርድ ቤት ይግባኝ ለማለት መብት አለዎት። RCW 34.05.542 (3) እና WAC 388-02-0645። በከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምገማ ከመጠየቅዎ በፊት በድጋሚ እንዲታይ ጥያቄ ማቅረብ አያስፈልግዎትም። DSHS የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምገማ ሊጠይቅ አይችልም። የከፍተኛ ፍርድ ቤት ግምገማ ጥያቄዎን እንዴት እንደሚስተናገድ መረጃ ለማግኘት እባክዎ WAC 388-02-0650 ይመልከቱ።

**ይህ ከተቀበሉት ሰነዶች ጋር ለማነፃፀር የሚያግዝዎትን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ምሳሌ ነው።**



ናሙና

**ዳግም እንዲታይ ጥያቄ (REQUEST FOR RECONSIDERATION)**

ስም፦ ____________________ የዶሴ ቁጥር። የጉዳይ ቁጥር

አድራሻ፦ ____________________ የኤጀንሲ ቁጥር። ____________________

____________________

ከተማ፦ ____________ ግዛት፦ ________ ዚፕ ኮድ፦ ____________

ስልክ:- ____________________

እባክዎ የመጨረሻው ትዕዛዝ በድጋሚ እንዲታይ ለምን እንደፈለጉ ያብራሩ። ተጨማሪ ገፆችን ሊያያይዙ ይችላሉ። ግልጽ ለመሆን ይሞክሩ። ለምሳሌ፣ የሚከተሉትን ያብራሩ፦

- ትዕዛዙ የተሳሳተ ነው ብለው ያሰቡት ለምንድን ነው (ከእሱ ጋር የማይስማሙት ለምንድን ነው)።
- ትዕዛዙ እንዴት መቀየር እንዳለበት።
- የአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ ሊያዩዋቸው የሚገቡ የተወሰኑ እውነታዎች አስፈላጊነት።

**በሚከተለው ምክንያት የአስተዳደራዊ ሕግ ዳኛ የመጨረሻውን ትዕዛዝ በድጋሚ እንዲያዩት እፈልጋለሁ፦**

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________

____________________ ____________________

ፊርማ ቀን

**ይህ ከተቀበሉት ሰነዶች ጋር ለማነፃፀር የሚያግዝዎትን አጠቃላይ መረጃ የሚሰጥ ምሳሌ ነው።**



ናሙና